በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 8


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon3@gmail.com


*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## ሰኔ ፬ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# ቁጣና የቤት ውስጥ ጥቃት

- **ዛሬ ሁላችንንም የሚመለከት አንድ ርዕሰ ጉዳይ እንመለከታለን። እርሱም ቁጣንና የቤት ውስጥ ጥቃትን የተመለከተ ነው።**
- **እስከዛሬ ድረስ በሕይወቱ ሳይቆጣ የኖረን ሰው ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነው።**
- **ቁጣ በተለያየ ምክንያት የሚከሰት ሲሆን ተቆጪነትም የተለያዩ ጉዳዮችን ጠቋሚ ነው።**
- **ጌታችን ቁጣን ከመግደል ጋር በማነጻጸር ገልጦታል። በብሉይ ዘመን የነበረውን የመግደልን ድርጊት ከቁጣ ጋር በሐዲስ አነጻጽሮታል።**
- *ማቴ 5፡21-26።*
- ‹‹ለቀደሙት። አትግደል እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል። እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ። አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ፤ ባላጋራ ለዳኛ እንዳይሰጥህ ዳኛም ለሎሌው፥ ወደ ወህኒም ትጣላለህ፤ እውነት እልሃለሁ፥ የመጨረሻዋን ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከቶ ከዚያ አትወጣም።››
- በብሉይ የሚገድል ሁሉ ይገደል ነበር።
- አንድ ሰው በውስጡ ሸምቆ በወንድሙ የሚቆጣ ከሆነ ይፈረድበታል። እንዲህ ያለውን ሰው ውስጡን እግዚአብሔር እንጂ ሰው ሊያነበው አይችልም።
- እግዚአብሔር እንደ ዝሙት ሁሉ መግደልንም ሆነ ቁጣን መርምሮ የሚመለከተው ከልባችንና ከአእምሮአችን ነው። መርምሮ አይቶንም እንደሥራችን ይፈርዳል።

# ቁጣና የቤት ውስጥ ጥቃት

- በተጨማሪም በርዕሳችን ዙሪያ ትዳርን አስመልክቶ በጣም አስፈላጊ የሆነውን መልዕክት እንመልከት፡፡
- *ኤፌሶን 4፡26-27 እና 31-32፡፡*
- ‹‹ ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ፤ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት፡፡ … መራርነትና ንዴት ቁጣም ጩኸትም መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ፡፡ እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፥ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ፡፡»
- ባልተግባባችሁበት ጉዳይ የተነሳ በመካከላችሁ ቁጣ ቢኖር ቁጣችሁን አብርዳችሁ አብራችሁ ለጸሎት በመቆም እስክትጸልዩ ድረስ እንደተቆጣችሁ ወደ መኝታችሁ አትሂዱ፡፡
- በርግጥ አድራችሁ የምትፈቱበት ሥርዓት ኖሮአችሁ ተስማምታችሁ ከሆነ መልካም ቢሆንም እያሰላሰላችሁት ግን ወደ መኝታችሁ አትሂዱ፡፡
- ምክንያቱም ከቁጣው ጋር ዲያቢሎስ ይኖራልና ነው፡፡ በሌላው ተቆጥቶ ይቅር ይል ዘንድ ያቃተው ሰው እንቅልፍ እንዴት አድርጎ ይወስደዋል? ይቅር አለማለታችን ራሱ ይቀሰቅሰናል፡፡
- ይቅር ማለት አለመቻል በስጋት የተሞላንና የታወክን ያደርገናል፡፡
- ስለዚህ ለመነጋገር የምንችልበት ጊዜ እንኳ ብናጣ ተቆጥተን ከመተኛት ይልቅ ከጌታችን የተማርነውን ይቅርታን አድርገን እናንቀላፋ፡፡
- ስለዚህ ዛሬ በአጭሩ ቁጣንና የቤት ውስጥ

# ለቁጣ የሚያነሳሱን ምክንያቶች

1. ደህንነታችንና ጥበቃችን የተነካ የተደፈርን ወይም የተጎዳን መሆን
    - ‹‹ይህን የምትመኪበትን መልክ አጠፋዋለሁ… ›› እያሉ መዛት…
    - አንዳንድ ጊዜ በከረረ ንግግር ውስጥ ‹‹እገልሃለሁ… እገልሻለሁ …›› ልንል እንችላለን፡፡ ይህ ዛቻ ለመግደል መሞከር፣ ወንጀልም ነው፤ ወደ ፍርድ ቤት ሊያስቀርበን ይችላል፤ በክርስትናም አልተፈቀደም፡፡
    - ስለዚህ የሌሎች ጸጥታና ደህንነት የተጠበቀ እንዲሆን አንደበታችንን/ምላሳችንን መጠበቅ ይገባናል፡፡
2. መብትን መጣስና ግጭት
    - መብትን መጣስ በሂደት ቁጣን ያስከትላል፡፡
    - አንዳንዴ ሳይታሰብ ይፈነዳል፡፡ ያም ነውጠኛነትን ሁከትን ያስከትላል፡፡
3. ሰውን መናቅ ወይም ማቃለል
4. ማስፈራራት፣ ማስደንገጥ፣ ግትርነት
5. የሰውን መብት መጣስ፡- በትዳር ባልም ሚስትም መብት ያላቸው ቢሆኑም አንዱ የላለውን አለማክበሩ፡፡
6. ጥብቅ ሥርዓትን/መመሪያን እሴቶችን መጣስ
    - የያዕቆብ ልጆች ጥብቅ ሥርዓታቸው/መመሪያቸውና እሴቶቻቸው ተጥሰው እህታቸው ዲና በተነካች ጊዜ ያ ሰው የሚያገባት ቢሆንም እንኳ ወንድሞችዋ ያደረጉትን እናስታውሳለን? ያገኙትን ሁሉ ገደሉ ይላል ቅዱስ መጽሐፍ…
    - በክርስቲያኖች ወይም በሕዝብ ዘንድ የታመነበትን መልካም ነገር የሚጥስ ሲገጥመን እንቆጣለን፡፡
    - ቅድስና የተለየውን ድርጊት የሚያስፋፋንም ሰው እንቃወማለን፡፡ ድርጊቱንም ለማውገዝ ራሳችንን ዋና ተዋናይ እናደርጋለን፡፡
    - እንዲህ ያለውን ነውር ነገር ከሚቃወሙም ጋር አንድነት ፈጥረን እንቆማለን ጥብቅ ሥርዓትንመመሪያና እሴት ተጥሶአልና፡፡

# ለቁጣ የሚያነሳሱን ምክንያቶች

7. ያልተሟላ ፍላጎት
    - አንድን ልጅ ያለአግባብ ዛሬ ምግብ አትበላም ብለን ብንከለክለው መቆጣቱ አይቀርም…
8. ለረጅም ጊዜ ያልተፈቱ ችግሮች
    - መለያየት፣ ፍቺ፣ ግኑኝነትን ማቋረጥ፣ ኃጢአት፣…
9. የአደንዛዥ እፅ ሱሰኝነት
10. የሰውነታችን ችግሮች፡- እንቅርት፣ የጭንቅላት እጢ… ቁጣን ያባብሳል፡፡

- ከላይ የተጠቀሱትም ሆኑ ሌሎችም በርካታ ምክንያቶች ለቁጣ ምንጭ ናቸው፡፡
- አሁንም ሆነ ከዛሬ በፊት ለቁጣ ምክንያት የሆኑንን ምክንያቶች እያንዳንዳችን እንፈልግ፡፡

## *ቁጣን መግለጫ መንገዶች ወይም የቁጣ ዓይነቶች*

1. ከማፈር፣ ከፍርሃት ወዘተ የተነሳ ነገሮች ለመሸፋፈን መሞከር ወይም ስንሞክር የምንቆጣው ቁጣ
2. ያበጠ ነገር ሲፈነዳ የሚከሰት፡- የት፣ መቼ፣ እንዴት፣ … ተናደድን? ማታ ደክመን ሳለ፣ የትዳር አጋራችንን ስናይ? ስንናደድስ ትንፋሽ ያጥረናል? ደም ሥራችን ይወጠራል? ጀርባችንን ያመናል?
3. አሁን ወይም ከዚህ በፊት በሆኑ ነገሮች በሌሎች መናደድ
4. በራስ መቆጣት ወይም መናደድ
5. በእግዚአብሔር መቆጣት  ወይም መናደድ

# የቁጣ ማከሚያ መንገዶች

1. የመቆጣት ወይም ቶሎ የመናደድ ችግር እንዳለብን አምነን መቀበል
2. የተናደድንባቸውን አጋጣሚዎች በማስታወስ የት፣ መቼ፣... ከማን ጋር ሁኔታችን ምን ይመስል እንደነበር ራሳችንን እናስታውስ
3. ራስን መቆጣጠር
   - ከቦታው ቶሎ ርቆ መሄድ
   - ተናደን ምንም ነገር ቶሎ ከመናገር አፋችንን መቆጠብ
   - ተናደን መኪና አለመንዳት ከሆነም ቀስ ብለን ማሽከርከር፣ እናንብብ፣ ... በአንድ ጉዳይ ራሳችንን እንጥመድ
4. ለምን እንደተናደድን እንግለጽ
5. ሊረዱን የሚችሉ መካሪዎች እንዲመክሩን ማድረግ
6. ይቅር ማለት
   - ይቅር ካልን ጉዳዩን ለእግዚአብሔር ሰጠን ማለት ስለሆነ አንጨቃጨቅ፣
   - ጌታችን በመስቀል ሆኖ ተቸንክሮ .. የሚያደርጉትን አያውቁምና ብሎ ይቅር እንዳለን እናስብ፡፡
7. በመንፈሳዊ ጎዳና የሚመሩን እንዲኖሩን መሆን
   - የንስሐ አባታችን ምክር ዘወትር የማይለየን እንሁን

# የቤት ውስጥ ጥቃትና ግጭት

1. የመቆጣት ወይም ቶሎ የመናደድ ችግር እንዳለብን አምነን መቀበል
2. የተናደድንባቸውን አጋጣሚዎች በማስታወስ የት፣ መቼ፣… ከማን ጋር ሁኔታችን ምን ይመስል እንደነበር ራሳችንን እናስታውስ
3. ራስን መቆጣጠር
   - ከቦታው ቶሎ ርቆ መሄድ
   - ተናደን ምንም ነገር ቶሎ ከመናገር አፋችንን መቆጠብ
   - ተናደን መኪና አለመንዳት ከሆነም ቀስ ብለን ማሽከርከር፣ እናንብብ፣ … በአንድ ጉዳይ ራሳችንን እንጥመድ
4. ለምን እንደተናደድን እንግለጽ
5. ሊረዱን የሚችሉ መካሪዎች እንዲመክሩን ማድረግ
6. ይቅር ማለት
   - ይቅር ካልን ጉዳዩን ለእግዚአብሔር ሰጠን ማለት ስለሆነ አንጨቃጨቅ፣
   - ጌታችን በመስቀል ሆኖ ተቸንክሮ .. የሚያደርጉትን አያውቁምና ብሎ ይቅር እንዳለን እናስብ፡፡
7. በመንፈሳዊ ጎዳና የሚመሩን እንዲኖሩን መሆን
   - የንስሐ አባታችን ምክር ዘወትር የማይለየን እንሁን

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org

... ክፍል ዘጠኝ ይቀጥላል፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡